## ለኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የአሳብ ፡ ማነሳሻ ፡ የሆኑት ፡ ምንጮች ።[ሀ]

ከረኔ ፡ ዳቪድ ።[ለ]

እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ እንዲሰናዱ ፡ ወሰኑ ። ሦስት ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ ዓዋቂዎች ፡ ሁለት ፡ ፈረንሣውያን ፡ ሦስተኛው ፡ ደግሞ ፡ ስዊስ ፡ የሆኑ ፡ ተመረጡ ። እንዲሁም ፡ በናፖሊዮኒክ ፡ የሕግ ፡ ዝግጅት ፡ (መሰናዶ) ፡ ተደርጐ ፡ እንደነበረው ፡ ሁሉ ፡ አምስት ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ለማዘጋጀት ፡ ሲባል ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ አዘጋጅ ፡ (የፍትሐ ፡ ነገሥት) ኮሚሲዮን ፡ እንዲቋቋም ፡ ተደረገ ። በመጀመሪያ፡ ተሠርቶ ፡ ያለቀው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሲሆን ፡ የታወጀውም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው[1] ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ደግሞ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታወጀ ። የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የንግድ ፡ ሕጎች ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ግንቦት ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታውጀው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉት ፡ ግን ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ መስከረም ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ማለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ መሠረት ፡ የ፲፱፻፶፫ ፡ ዓመት ፡ የመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ነው[2] ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፷፭ ፡

---

ሀ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ በሬቪ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ・ ም ・ ፪፻፶፯—፫፻፲፪ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል ። ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ የተረጐሙት ፡ ማይክል ፡ ኪንድረድ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰርና ፡ ረዳት ፡ ዲን ፡ ናቸው ።

በአረብኛ ፡ ቁጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻዎች ፡ አንቀጹ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ በተጻፈበት ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ ናቸው ። በተርጓሚው ፡ የተጨመሩት ፡ ግን ፡ በሆሄዎች ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።

የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዳቪድ ፡ ሶሲቲ ፡ ደ ፡ ሌጂስላሲዮን ፡ ኮምፓሬ ፡ መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለሰጡት ፡ ንግግር ፡ የተዘጋጀው ፡ ነው ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሰናዶ ፡ በፕሮፌሰር ፡ ዳቪድ ፡ የተዘጋጁ ፡ ሌሎች ፡ አንቀጾች ፡ የሚቀጥሉት ፡ ናቸው ። "የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጣዊ ፡ አቀዋውምና ፡ ከሌሎችም ፡ አገሮች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጎች ፡ የሚለይበት ፡ ሁኔታ" ፡ ዘይትስ ፡ ክሪፍት ፡ ፋር ፡ አውስላንዲስ ፡ እንድ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ፕሪቫትሬሽ ፤ የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (በፈረንሣይኛ) ፡ "ለኢትዮጵያ ፡ የተዘጋጀ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ—ለአፍሪካ ፡ አገሮች፡በሚደረገው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሰናዶ ፡ መታወስ ፡ የሚገባቸው ፡ ጉዳዮች" ፡ ቱሌን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፤ ፲፱፻፶፱(በእንግሊዝኛ) ። በተጨማሪ ፡ "የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሻሻል ፡ በአፍሪካ ፡ አገሮች" ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ ሪቩል ፡ ፔናን ፡ ፲፱፻፷፬ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዳቪድ ፡ በዳካር ፡ የሰጡትን ፡ አስተያየቶች ፡ ይመለከቷል ።

ለ በፓሪስ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የሕግ ፡ ፕሮፌሰር ።

1. ሳንተር ፡ ፍራንሴ ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ኮምፓሬ ፡ በተባለው ፡ ድርጅት ፡ አማካኝነት ፡ በፈረንሳይኛ ፡ የተጻፈው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሕጉን ፡ መጀመሪያ ፡ ባረቀቁት ፡ የስዊስ ፡ ዜጋ ፡ በሆኑት ፡ አማካሪ ፡ ከተዘጋጀው ፡ መግቢያ ፡ ጋር ፡ በኑቬል ፡ ኮሎክስዮን ፡ ዱ ፡ ኮሚቴ ፡ ደ ሌጂስላሲዮን ፡ ኤትራንጀር ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ታትሟል ።

2. የፍትሐ፡ብሔር ፡ ሕግና ፡ የንግድ፡ሕግ፡የኢትዮጵያ፡ኦፊሴላዊ ፡ የሕግ ፡ ጋዜጣ ፡ በሆነው፡በተሰይ ፡ በወጣው ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በአማርኛ፡ታትሞ፡ሲወጣ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ አብሮ ፡ በዚሁ ፡ ጋዜጣ ፡ ወጥቷል ። እነዚሁ ፡ ሕጎች ፡ በፈረንሳይኛ ፡ በሊብሬሪ ፡ ጀኔራል ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ጁሪስፕሩዳንስ ፡ አማካኝነት ፡ ታትመው ፡ ወጥተዋል ።

ዓ ፡ ም ፡ በድንጋጌ ፡ መልክ ፡ ታውጆ ፤ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፓርላማ ፡ ጸደቀ ።

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዶራሲ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ዝግጅት ፡ ረገድ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የአማካሪነት ፡ ክብር ፡ ነበረው ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ እናዋያችኋለን ። የሕጉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ምን ፡ ምን ፡ ነገሮችን ፡ እንደተመለከቱ ፡ የትኞችን ፡ እንደተገለገሉባቸው ፡ እስከ ፡ ምን ፡ ድረስና ፡ በምንስ ፡ መንገድ ፡ የአንዳንድ ፡ አገሮችን ፡ ሕጐችና ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ እንደተጠቀሙባቸውና ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ እስከ ፡ ምን ፡ ድረስና ፡ በምንስ ፡ መንገድ ፡ ኢትዮጵያ—በቀል ፡ በሆኑ ፡ ጽንስ—አሳቦች ፡ ለመጠቀምና ፡ ከነዚህ ፡ አሳቦች ፡ ጋር ፡ የተያያዙትን ፡ ደንቦችና ፡ ልምዶች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ውስጥ፡ ለማስገባት ፡ እንደሞከሩ ፡ እንገልጻለን ።

የሕጉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የተጣለባቸውን ፡ ተግባር ፡ እንዴት ፡ እንደተመለከቱትና ፡ የችግሩን ፡ (ፕሮብሌሙን) አካባቢ ፡ ለመርዳት ፡ ያህል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ መሰናዶ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ሁኔታ ፡ ባጭሩ ፡ መግለጽ ፡ ያስፈልጋል ።

የሕጉ ፡ መሰናዶ ፡ በተጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ቅጥ—አጣሽ ፡ ብዙውንም ፡ ጊዜ ፡ ለማወቅ ፡ አስቸጋሪና ፡ ከስፍራ ፡ ወደ ፡ ስፍራ ፡ የሚለያይ ፡ ነበር ። በጣም ፡ ጥቂት ፡ ከሆኑ ፡ ሕጐች ፡ በስተቀር[3] ፡ የተሰናዱ ፡ ሕጐች ፡ አልነበሩም ፤ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ የያዙ ፡ ወይም ፡ ሕጉን ፡ የሚያብራሩ ፡ ጽሑፎች፡ አልነበሩም ።

አንድ ፡ አገር ፡ የተሰናዱ ፡ ሕጐች ፤ ድንጋጌዎች ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ የያዘ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ተቀባይነት ፡ ያለው ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሳይኖረው ፡ ሲቀር ፡ እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ አገር ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ አለው ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አባባል ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሁኔታ ፡ በትክክል ፡ የሚገልጽ ፡ አይሆንም ።

እስከ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒሊክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሕግ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ እንድትተዳደር ፡ የአገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ከልክሏት ፡ ነበር ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፤ ጠብ ፡ አጫሪ ፡ በሆኑ ፡ ጐረቤቶች ፡ እና ፡ በተፈጥሮ ፡ መቅሰፍቶች ፡ የተነሳ ፡ በየጊዜው ፡ በስጋት ፡ ላይ ፡ ስለነበር ፤ እንደ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ መቀጠሉ ፡ ባሰጋበት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ዋናው ፡ አሳሳቢ ፡ ጥያቄ ፡ የሕዝቡን ፡ አንድነት ፡ መጠበቅ ፡ ነበር ። ይህ ፡ አንድነት ፡ የተጠበቀው ፡ በሕግ ፡ አሳብ ፡ በመመካት ፡ ሳይሆን ፤ ስምምነትንና ፡ ፀጥታን ፡ ያሰፍናሉ ፡ ተብለው ፡ በታለሙ ፡ በርትዕ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ የርትዕ ፡ ደንቦች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉት ፤ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዘፈቀደ ፡ በሚሠሩት ፡ በአገሬው ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ሽምግልና ፡ ነበር ።

---

3. የግለ ፡ ሰብ ፡ ሕጐች ፡ የሚከተሉት ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ፡ "የብድር ፡ ሕግ ፤" የ፲፱፻፳፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የዜግነት ፡ ሕግና ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ። የኤን ፡ ማሪንን ፡ ዘ ፡ ጁዲሻል ፡ ሲስተም ፡ አንድ ፡ ዘ ፡ ሎውስ ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮፒያ ፡ (፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡) የሚለውን ፡ ይመለከቷል ። የብድርና ፡ የይርጋ ፡ ሕጐች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተሽረዋል ፡ (ቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯) ።

ሽማግሌዎቹ ፡ ውሳኔዎቻቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ የአገሩ ፡ ሰዎች ፡ በተፈጥሮ ፡ የሚ ከተሏቸውን ፡ ልማዶች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቢመለከቱም ፡ ልማዶቹ ፡ እንደ ፡ ደንበኛ ፡ ሕግ ፡ ኃይል ፡ የላቸውም ፡ ነበር ። ልማዶቹ ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ላይ ፡ የማላመን ፡ እንጅ ፡ የማስገደድ ፡ ኃይል ፡ የላቸውም ፡ ነበር ። ኢትዮጵያን ፡ ባሕላዊ ፡ ሕግ ፡ አላስተዳደራትም ።

እንዚህ ፡ የሕግ ፡ አስገዳጅነት ፡ ሳይኖራቸው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉት ፡ የል ማድ ፡ ደንቦች ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ ይለያዩ ፡ ነበር ። ደንቦችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ምንም ፡ የተወሰደ ፡ እርምጃ ፡ አልነበረም ። በተጨማሪም ፡ በመልክ ፡ በመልካቸው ፡ ስላልተገለጹ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለማረጋገጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበሩ ። በደንቦቹ ፡ ሥራ ፡ የሚተዳደረው ፡ ጉዳይና ፡ የደ ንቦቹ ፡ ውጤት ፡ አጠራጣሪ ፡ ነበር ፡ በምን ፡ ሁኔታም ፡ አስገዳጅነት ፡ እንዳላ ቸው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ያልተጣራ ፡ ነበር ።

በኤርትራ ፡ ክፍለ ፡ አገር ፡ የየሥፍራውን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ ለማመልከት ፡ ሲባል ፡ በኢጣሊያ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተደርገው ፡ የነበሩት ፡ ጥናቶች ፡ በየሥ ፍራው ፡ ያለውን ፡ የልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ ልዩነትና ፡ አለማረጋገጥ ፡ እንዲሁም ፡ ሕጋዊ ፡ ካልሆኑ ፡ የሕብረ ፡ ሰብ ፡ ጠባዮችና ፡ የቅን ፡ ልቦና ፡ አሠራር ፡ ደንቦች ፡ የተለየ[4] ፡ አስገዳጅነት ፡ ያለው ፡ የልምዳዊ ፡ ሕግ ፡ ጽንሰ—አሳብ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ አለመኖሩን ፡ ያሳያሉ ። በመጨረሻም ፤ ልንገነዘበው ፡ የሚገባ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ በተለይም ፡ ባለፉት ፡ ፱ ፡ ዓመታት ፡ የልማድ ፡ ደንቦችን ፡ ለማረጋ ገጥ ፡ የተደረገ ፡ ድካም ፡ ባለመኖሩ ፡ ምክንያት[5] ፡ ደንቦቹ ፡ በጣም ፡ ያልተረ ጋጉ ፡ መሆናቸውን ፡ ነው ።

ኢትዮጵያውያን ፡ የሕግ ፡ አሳብን ፡ በብዛት ፡ ተለያይተውና ፡ ሁልጊዜም ፡ አከራካሪ ፡ ሆነው ፡ ከሚገኙት ፡ የልማድ ፡ ደንቦች ፡ ጋር ፡ ሳያገናኙ ፡ ታላቅ ፡ ዕውቀትንና ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ ክብርን ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ፡ ከሚባሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ጋር ፡ አጣምረውታል ። የእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ያላቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቢያ ንስ ፡ በአሳብ ፡ (በቲወሪ) የተቀደሰ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚያምኑበትን ፡ የእስላም ሃይማኖትን ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ብንተወውም ፤ ኢትዮጵያውያን ፡ ክርስቲያኖች በ፲፫ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ አል ፡ አሳድ ፡ ኢባን ፡ አል ፡ አሳል ፡ በተባለ ፡ ግብፃዊ ፡ ሊቅ ፡ ተረቅቆ ፡ በ፲፯ኛው ፡ ወይም ፡ በ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ፡ ዘመን ፡ ከአረብኛ ፡ የኮፕቲክ ፡ ክርስቲያን ፡ ቋንቋ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ የተተረጐመውን ፡ መጽሐፍ ፡ በሃይማኖት ፡ ደንቦች ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ሥል ጣን ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ይቀበላሉ ። ይህ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ (የንጉሦች ፡ ፍትሕ) የተባለው ፡ የሕጎች ፡ ጥርቅም ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ይጠቀስ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መደበኛ ፡ ቋንቋ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ተተርጉሞና ፡ በኢትዮጵያ ፡

---

4. በራሴኛ ፡ ደ ፡ ለቱዲ ፡ ኢትዮፒቺ ፡ የሚገኙትን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ በተለይም ፡ ከንሰቱዲኒ ፡ ጊሪዲኬ ፡ ዴል ፡ ሰራይ ፡ (የአር ፡ ኤስ ፡ ኢ ፲ በልዩም ፡ ፲፩፤ ፲፱፻፵፩ ዓ ፡ ም ፡ ገጽ ፡ ፻፭፬-፻፫፲፫ ፡ አባሪ) ።

5. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አርእስት ፡ ያላቸው ፡ በሁለት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጸሐ ፊዎች ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ ማነጻጸር ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። አንዱ ፡ ዝነኛ ፡ አንትሮፖሎጂስት ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ በመሆናቸው ፡ ሁለቱ ፡ ለሰጡት ፡ የተለያየ ፡ አገላለጽ ፡ ከብዙ ዎች ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።
በኋላ ፡ ባሕል ፡ በየስምንት ፡ ዓመት ፡ እያገናኙ ፡ በአንድ ፡ እድሜ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ አዲስ ፡ ትውልድ ፡ ለሥልጣን ፡ አዳም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የጋላ ፡ ባህላዊ ፡ ሕግ ፡ ተደግሞ ፡ ሲነገር ፡ ለወጥ ፡ ያለ ፡ ይመስላል ።

ውስጥ ፡ ታትሞ ፡ እስማወቁ[6] ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ዳኞች ፡ ባልተለዋወጠ ፡ አኳ ኋን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አውለውት ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ ያጠራጥራል ። ሆኖም ፡ ልንገነ ዘበው ፡ የሚገባን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚደረገው ፡ ክብር ፡ የሚገለጸውን ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ ነው ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ በልማዳቸውና ፡ በሥራቸው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱን ፡ ትእ ዛዝ ፡ በጥብቅ ፡ ባይከተሉም ፡ ቅሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ የሚቆ ጥሩት ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ለነርሱ ፡ ሕጉ ፡ የሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሚሰጡ ት ፡ ውሳኔዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ እነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ ለጊዜው ፡ አስፈላጊ ፡ ሁናቴ ፡ የሚስማሙና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውሉ ፡ መሆን ፡ ስላለባ ቸው ፡ ነው ። ወይም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ በእርግጥ ፡ ሊተን በይ ፡ ቢችል ፡ ሕጉ ፡ ዳኞች ፡ ወደፊት ፡ በሚነሱ ፡ የክስ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የሚሰ ጡት ፡ ውሳኔ ፡ አይደለም ። በኤውሮፓ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ መሰናዶ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ እንደነበረውና ፡ በእስላሞች ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ ለኢትዮጵያ ውያን ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከሚውሉ ፡ ነገሮች ፡ ርቆ ፡ የሞራል ፡ ሁናቴ ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። ሕግ ፡ ማለት ፡ ከሃይማኖት ፡ የሞራል ፡ ትእዛዞች ፡ ጋር ፡ በቅርብ ፡ ተያ ይዞ ፡ የሚገኝ ፡ የሕብረ—ሰብ ፡ ደንብ ፡ ነው ። ልማዶችና ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳ ኔዎች ፡ ከሕጉ ፡ ጋር ፡ አለመስማማታቸው ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ አያስገርማቸ ውም ። የልማዶችና ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ከሕግ ፡ ጋር ፡ አለመስማማት ፡ የሚያሳየው ፡ (ይህን ፡ ማሳየት ፡ አስፈላጊ ፡ ባይሆንም) ሕብረ ፡ ሰብ ፡ ፍጹም ፡ አለመሆኑን ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታመናል ። ኢትዮጵያውያንን ፡ የሚያስገርማ ቸው ፡ የራሳቸው ፡ የሆነውን ፡ ግን ፡ የሚያስወቅስ ፡ መሆኑን ፡ በጣም ፡ የሚያው ቁትንና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የሚያዝኑበትን ፡ ጠባያቸውን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የልማድ ፡ ደንቦችን ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ አውጥቶ ፡ እንዲከተሉ ፡ ሲያዛቸው ፡ ነው ። ኢትዮጵያውያን ፡ ሕግን ፡ እንዴት ፡ እንደሚያዩት ፡ ለመረዳት ፡ ያህል ፡ ደንቦች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በመዋል ረገድ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዘንድ ፡ ተፈጻሚ ነት ፡ እንዳላቸውና ፡ እንደሌላቸው ፡ ለመግለጽ ፡ ሳይጠብቡ ፡ እስከ ፡ ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የአውሮፓ ፡ ዩኒቨርሲቲዎች ፡ በሙሉም ፡ ባይሆን ፡ በብ

---

ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ በኤ ፡ አርኖልድ ፡ አማካኝነት ፡ ሊብሬ ፡ ኢትዮፒቺ ፡ ተብሎ በሀል ፡ በ፲፰፻፵፩ ፡ ዓ፡ም ፡ ሲታተም ፡ በባክማን ፡ አማካኝነት ፡ ደግሞ ፡ ኮርፐስ ፡ አዩሪስ ፡ ኢትዮ ፒቺ ፡ ተብሎ ፡ በ፲፰፻፺፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በበርሊን ፡ ታትሟል ። ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ዋና ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ እትም ፡ በኢጣሊያ ፡ በ፲፰፻፺፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታወቀው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ሊቅ ፡ በኢግናዚዮ ፡ ጉይድ ፡ የግእዙ ፡ ጽሑፍና ፡ የጣልያንኛው ፡ ትርጉም ፡ ተጣምሮ ፡ ተዘጋጀ ። እር እሱቱም ፡ ኢል ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኦ ፡ ሌጂዝላዚዮኔ ፡ ዴ ፡ ሬ ፤ ኮዲቼ ፡ ኤክሊዚያስቲኮ ፡ ኤ ቺቪሌ ፡ ዲ ፡ አቢሲኒያ ፤ ተራዶቶ ፡ ኤ ፡ አኖታቶ ፡ ነው ። ዋናነቱ ፡ እላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ እትም ፡ አንስ ፡ ያለው ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ መርምሮ ፡ አሳቡን ፡ አሳጥሮ ፡ የሚገልጽና ፡ የሃሳብ ፡ ቅድም ፡ ተከተል ፡ ባለው ፡ ድርጅት ፡ በሮቤርቶ ፡ ሮሲ ፡ ካኔባሪ ፡ አማካኝነት ፡ በጣልያንኛ ፡ በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ (ኢል ፡ ሊብሮ ፡ ዲ ፡ ሬ) ፡ ኮዲቼ ፡ ዴሎ ፡ ሌጂ ፡ አቢሲኔ ፡ ኮንናቴ ፡ ኤ ፡ ሬሪሜንቲ ፡ አል ፡ ዲሬቶ ፡ ኢታሊያኖ ፡ ተብሎ ፡ ታተመ ።

የተርጓሚ ፡ ማስታወሻ ፦ በእርግጥ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የተደረጉ ፡ ምርምሮች ፡ እንደሚያመለ ክቱት ፡ ለማስተማርያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ በግዕዝ ፡ የተጻፉ ፡ በአማርኛ ፡ ትርጉምና ፡ ትችት ፡ የያዙ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ብራናዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለብዙ ፡ መቶ ፡ ዘመናት ፡ በሕ ዝብ ፡ ዘንድ ፡ ይገኙ ፡ ነበር ፡ የዚህ ፡ ብራና ፡ እትም ፡ ልክ ፡ ከ፲፱፻፷፩ (እ. ኤ. አ.) በፊት ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መልካም ፡ ፈቃድና ፡ ትእዛዝ ፡ ታትሞ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ እትሙ ፡ ሳይጠረዝ ፡ በጣሊያን ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ ወድሟል ። በ፲፱፻፷፭(እ.ኤ.አ.)የአዲስ ፡ አበባ ፡ የብርሃ ንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ የዚህን ፡ ፎቶ ፡ አፍሴት ፡ እሳትሞ ፡ አውጥቷል ።

ዛት ፡ በትምህርት ፡ መልክ ፡ ይሰጡ ፡ የነበሩትን ፡ ተምኔታዊ ፡ (አይዲል) ሕግ ፡ ማለት ፤ የሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ (ናቹራል) ፡ ሕግ ፡ ማስታወስ ፡ ብቻ ፡ ይበቃል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ሊጋል ፡ ፖሲቲቪዝም ፡ (ማለት ፤ ሕግ ፤ ሰው ፡ የሚያወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ እንጂ ፡ የተፈጥሮን ፡ ወይም ፡ የሞራልን ፡ ሕግ ፡ አይጨምርም ፡ ለሚለው ፡ አሳብ) በአንድ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ እንድንርቅ ፡ ቢያደርገንም ፤ አሁን ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲዎቻችን ፡ ውስጥ ፡ የሶሻል ፡ ሳይንሶች ፡ ትምህርት ፡ መዳበር ፡ በጠምዛዛ ፡ መንገድ ፡ ወደዚህ ፡ የሕግ አሳብ ፡ በፍጥነት ፡ እንድንመለስ ፡ ያደረገን ፡ ይመስላል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚታየው ፡ አቃፊ—ደጋፊ ፡ (ፕሮቪደንሻል) ወደ ፡ ሆነ ፡ መንግሥት ፡ ለመራመድ ፡ ያለው ፡ ጉዞ ፡ በተለይም ፡ አዲስ ፡ በሆነና ፡ ፍትሕ ፡ በተመላበት ፡ አኳኋን ፡ ሕብረ ፡ ሰብን ፡ ለማደራጀት ፡ የሚደረገው ፡ የሶሻሊስት ፡ አገሮች ፡ ጥረት ፡ ሕጉ ፡ ልማዶችንና ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ያሉትንና ፡ በጊዜው ፡ የሚገኙትን ፡ የኑሮ ፡ ግንኙነቶች ፡ ብቻ ፡ መመልከት ፡ የለበትም ፡ ወደሚባለው ፡ አሳብ ፡ መልሶናል ። ሕግ ፡ ሕብረ ፡ ሰብን ፡ መለወጥ ፡ ስላለበት ፡ አሁን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በመዋላቸው ፡ ምክንያት ፡ ተከብረው ፡ ከሚገኙት ፡ ደንቦች ፡ በመቅደም ፡ መጪውን ፡ ተመልካች ፡ መሆን ፡ አለበት ። ሕጉም ፡ ልማዶችን ፡ ማስተጋባትና ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ቦታ ፡ እንዲይዙ ፡ የማድረግ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ እንዳለው ፡ ሆኖ ፡ መታየት ፡ የለበትም ።

ይህ ፡ አሳብ ፡ በበለፀጉ ፡ አገሮች ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ በብልጽግና ፡ ከምዕራባውያን ፡ አገሮች ፡ አንሰው ፡ ከሚገኙት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በተለይም ፡ የአገሩ ፡ መሪዎች ፡ ይህንን ፡ የብልጽግና ፡ መራራቅ ፡ ለማጥፋት ፡ ሲሉ ፡ ለውጥ ፡ ለማምጣት ፡ በሚደክሙበት ፡ ኢትዮጵያን ፡ከመሰለ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በይበልጥ ፡ እውነት ፡ መሆን ፡ አለበት ። የሕጉ ፡ መሰናዶ ፡ ሥራ ፡ ልማዶችን ፡ መቀበልና ፡ እነርሱንም ፡ በማዋሃድ ፡ ደንቦችን ፡ ማርቀቅ ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ባህል ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ተጠብቆ ፡ ይቀር ፡ ነበር ። በእርግጥ ፡ እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሥራ ፡ የባሕልን ፡ ተምኔታዊነት ፡ (አይዲያልዝም) ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ትቶ ፡ በእውነቱ ፡ ባሕልን ፡ ጭራሽ ፡ ያልተከተለ ፡ ይሆን ፡ ነበር ። በአንትሮፖሎጂ ፡ ጥናት ፡ የተገኘውን ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ እንዲወጣ ፡ ቢደረግ ፡ ኖሮ ፡ በአሮጌው ፡ ባሕል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ተራ ፡ ነገር ፡ ማሻሻል ፡ ቀርቶ ፡ እንደነበረ ፡ እንዲቀጥል ፡ ማድረግ ፡ ይሆን ፡ ነበር ።

ስለዚህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዥ ፡ ሕጎችን ፡ በተለይም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ ለማቋቋም ፡ በወሰኑ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባሕል ላይ ፡ ብቻ ፡ እንዲመሠረት ፡ አላሰቡም ፡ ነበር ። ገዥው ፡ የፈለጉት ፡ የአውሮፓ ፡ አህጉር ፡ የሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ በ፲፱ኛውና ፡ በ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ በድሮ ፡ ጊዜ ፡ የሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ያበረከተውን ፡ ተምኔታዊ ፡ መሠረት ፡ ለማደስ ፡ እንዳሰቡ ፡ ሁሉ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የታሰበውን ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዲስ ፡ እትም ፡ የሚቆጠር ፡ ሕግ ፡ ነበር ።

በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በአውሮፓ ፡ የዚህ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ገለጻ ፡ ከግሎሴተርስ ፡ እስከ ፡ ፖንዲክቲስትስ ፡ በነበሩት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ የሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ት/ቤቶች ፡ ሊቃውንት ፡ በደንብ ፡ የተዘጋጀ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የፖለቲካ ፡ ሥነ ፡ ጥበብንና ፡ የየሥፍራዎችን ፡ ልማዶች ፡ ካጠኑ ፡ ሰዎች ፡ እርዳታ ፡ አግኝቶ ፡ ነበር ። በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ዝግ

ጅት ፡ ሊገኝ ፡ ባለመቻሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ ደንቦች ፡ ሊደነገጉ ፡ ይገባ ፡ እንደሆነ ፡ ለመወሰን ፡ ሲባል ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ሳይንስና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ሕግ ፡ መመልከት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ።

ይህን ፡ ማድረጉ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ አደጋ ፡ ነበር ። ይኸውም ፤ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ባዕድ ፡ ይሆንባታል ፤ በተጨማሪም ፡ ምንም እንኳ ፡ ሕጉ ፡ የተደነቀ ፡ ሥራ ፡ ሊሆን ፡ ቢችልም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሳይውል ፡ እንደቀረ ፡ ሁሉ ፡ አዲሱ ፡ ሕግም ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሳይውል ፡ ሊቀር ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ነበር ። የሕጉ ፡ ደራሲዎች ፡ ይህን ፡ አደጋ ፡ ተገንዝበውት ፡ ነበር ፤ ስለዚህም ፤ ሊሻሻሉ ፡ የሚገባቸውን ፡ ልማዶች ፡ ሕግ ፡ ሆነው ፡ እንዲወጡ ፡ ከማድረግ ፡ ይልቅ ፤ የግሥጋሴ ፡ ጠባይ ፡ ቢኖረውም ወይም ፡ ከዚህ ፡ የግስጋሴ ፡ ጠባዩ ፡ የተነሳ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕግ ፡ የሚሰኝና ፡ ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ወደፊት ፡ የሕግን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ ሊመራ ፡ የሚችል ፡ ሥራ ፡ ለመፍጠር ፡ ፈለጉ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጹት ፡ ሐሳቦች ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የአገር ፡ ውስጥና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ምንጮች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አስፈላጊና ፡ ሥራቸውም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ያስረዳሉ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አዲሱን ፡ ሕግ ፡ ለማርቀቅ ፡ የፈለጉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ፍትሕን ፡ የተመረኰዘ ፡ መስሎ ፡ በሚታያቸው ፡ አስተሳሰብ ፡ መሠረት ፡ ቢሆንም ፡ ሕጉ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ሊውል የሚችል ፡ እንዲሆን ፡ ደከመዋል ። ስለዚህም ፡ በተነጻጻሩ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ሕጎች ፡ በመጠቀም ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ልማዶች ፡ ለማሻሻል ፡ ዘመናዊ ፡ ለማድረግ ፡ እና ፡ ለማሟላት ፡ ሞክረዋል ።

የሕጉ ፡ መሠረት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ፡ ፍትሕ ፡ ያላቸው ፡ ስሜት ፡ ነው ። በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ስሜት ፡ የሚጥስ ፡ አንድም ፡ ደንብ ፡ አይገኝም ። በውጭ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ አዋቂ ፡ ተዘጋጅተው ፡ በመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በሕጉ ፡ አዋቂ ፡ አስተያየት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጠቃሚና ፡ ፍትሕን ፡ የተመረኰዙ ፡ ቢሆኑም ፤ የኢትዮጵያውያንን ፡ ፍትሕ ፡ ስሜት ፡ ተቃራኒ ፡ መስለው ፡ በታዩ ፡ ጊዜ ፡ ይወገዱና ፡ ይለወጡ ፡ ነበር ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ስለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አሠራር ፡ ጥቂት ፡ ምሳሌዎችን ፡ እንሰጣለን ።

ስለ ፡ ውርስ ፡ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በመጠኑ ፡ ዋና ፡ የሆኑ ፡ የውርስ ፡ መብቶችን ፡ በሕይወት ፡ ላለው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ። ኢትዮጵያውያን ፡ ንብረት ፡ በሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ መቅረት ፡ አለበት ፡ ከሚለው ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ ስለተቃረኑ ፤ መብት ፡ የሚሰጡት ፡ ደንቦች እንዲሰረዙ ፡ አስፈለገ ። ሟቹ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ከቤተሰቡ ፡ ያመጣውን ፡ ንብረት ፡ በሕይወት ፡ ባለው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ሊወረስ ፡ አይችልም ። የሟቹ ፡ ዘመዶች ፡ ባይኖሩም ፡ እንኳ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ አይወርሱም ፤ መንግሥት ፡ ቢወርስ ፡ ይመረጣል ።

ባለንብረት ፡ አለመሆኑን ፡ እያወቀ ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ ባይሆንም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ አዝርዕትን ፡ የሚዘራ ፡ ዛፎችን ፡ ለሚያተክል ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ነገርን ፡ የሚገነባን ፡ ሰው ፡ የሚደግፉ ፡ ብዙ ፡ ደንቦች ፡ በመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ ነበር ። ስለማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችም ፡ ይዞታን ፡ ፈቅዶ ፡ ነበር ። መሬት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ እንዳይከፋፈል ፡ በማለትም ፡ የጕረ

ቤት ፡ ሰዎች ፡ በቀዳሚነት ፡ የመግዛትን ፡ መብት ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። እነዚህ፡ ሁሉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በብዛት ፡ ተለወጡ ። ምክንያቱም ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረትን ፡ በጥብቅ ፡ ከሚወዱትና ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ አያጣም ፡ ከሚሉት ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ስሜቶች ፡ ጋር ፡ ባለመስማማታቸው ፡ ነው ።

የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ አደጋውን ፡ ያደረሰው ፡ የሌላውን ፡ ሰው፡ መኪና ፡ የሠረቀው ፡ ሌባ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ኃላፊነቱ ፡ የመኪናው ፡ ባለሃብት ፡ እንዲሆን ፡ ሲል ፡ ደንግጎ ፡ ነበር ። የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ጸሐፊ እንደሚከተለው ፡ ተከራከሩ ። የመኪናው ፡ ባለሃብት ፡ የኃላፊነት ፡ ኢንሹራንስ፡ እንዲይዝ ፡ ይገባዋል ። የኢንሹራንሱ ፡ የመግቢያ ፡ ዋጋው ፡ ሌባ ፡ ባደረሰው ፡ አደጋ ፡ የሚመጣውን ፡ ኪሣራ ፡ በመሸፈኑ ፡ ምንም ፡ አይቀጥልም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ኃላፊነቱ ፡ አደጋውን ፡ ባደረሰው ፡ ሌባ ፡ ላይ ፡ ይሁን ፡ ቢባል ፡ አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ለደረሰበት ፡ አደጋ ፡ ኪሣራውን ፡ ሳያገኝ ፡ ሊቀር ፡ ይችላል ። ለነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ እንዳችም ፡ መልስ ፡ ሊሰጥ ፡ ሳይችል ፡ ቢቀርም ፡ እነዚሀ ፡ ምክንያቶች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ፡ ፍትሕ ፡ ያላቸውን ፡ ስሜት ፡ በጣም ፡ ስለተቃወሙ ፡ ይህን ፡ ጥፋት ፡ የሌለበት ፡ የኃላፊነት ፡ ጉዳይ ፡ ለመቀበል ፡ ስላልተቻለ ፡ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረዝ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።

በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በምዕራባውያን ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ የማይገኘውን ፡ ጥፋት ፡ ሳይኖር ፡ ኃላፊነት ፡ የመግባት ፡ ጉዳይ ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ አሳቦችና ፡ ልማዶች ፡ ጋር ፡ ተስማምቶ ፡ በመገኘቱ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ ተደረገ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ጥፋት ፡ የሌለበት ፡ ቢሆንም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ እንደሆነ ፡ ጉዳት ፡ ለደረሰበት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለቤተሰቦች ፡ ኃላፊነት ፡ አለበት ። ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ ሕጉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ስሜቶች ፡ ጋር ፡ መስማማት ፡ አለበት ፡ በማለት ፡ የሕጉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያስገቡት ፡ ነው ።

ሌሎች ፡ ብዙ ፡ ምሳሌዎችን ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ። እነርሱም ፡ የሚገኙት ፡ አብዛኛውን ፡ በሕጉ ፡ የመጀመሪያው ፡ ሦስት ፡ መጻሕፍት ፡ (ማለት ፡ ስለ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፤ ስለውርስና ፡ ስለ ፡ ንብረት) ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፤ እንዲሁም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርሰው ፡ አላፊነት ፡ በሚገልጸው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። እነዚህን ፡ የሕጉን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ማንበብ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ፡ እውነትም ፡ ከምዕራብ ፡ አውሮፓ ፡ አገሮች ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ለምትለየው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የተጻፈ ፡ መሆኑን ፡ እራስን ፡ ማሳመን ፡ ነው ። በቀድሞው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትና ፡ በአዲሱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ለማየት ፡ እነዚህን ፡ ክፍሎች፡ማንበብ፡ይቀላል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ እነዚህ ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕብረ ፡ ሰብ ፡ ቢያስተጋቡም ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚገኙትን ፡ የልማድ ፡ ደንቦች ፡ እንዲሁ ፡ ያለማመዛዘን ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ አያወጣቸውም ። ይልቁንስ ፡ እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በልማድ ፡ ደንቦች ፡ በመገልገል ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚያስገሰግሰን ፡ እርምጃ ፡ ለመውሰድና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕብረ ፡ ሰብም ፡ ወደ ፡ በሰፀገ ፡ ደረጃ ፡ ለመምራት ፡ ይደክማሉ ። በጸሐፊውም ፡ አስተያየት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕብረ ፡ ሰብ ፡ በበለጠ ፡ ከፍትሕ ፡ ጋር ፡ እንዲዛመድ ፡ ያደርጋሉ ።

ይህ ፡ አሳብ ፡ ምን ፡ ውጤት ፡ እንዳለው ፡ ለማየት ፡ ስለመፋታት ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ምሳሌ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የሃይማኖትን ፡ ጋብቻ ፡ ብቻ ፡ ስለሚያውቅና ፡ ስለዚህም ፡ መፋታትን ፡ ስለሚከለክል ፡ በመፋታት ፡ በኩል ፡ ሕጉ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ አይከተልም ። የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ ብዛት ፡ አነስተኛና ፡ የሚፈጸመውም ፡ በስተእርጅና ፡ መሆኑን ፤ መፋታት ፡ ደግሞ ፡ ድካም ፡ አልባ ፡ መገኘቱን ፡ እንዲሁም ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ መፋታት ፡ መድረሱን ፡ በልማድ ፡ እንዳለ ፡ ሳይመለከቱ ፡ ቢቀሩ ፡ ሥራቸው ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂዎች ፡ አሰቡ ። ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ መፋታት ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ብሎ ፡ በወተወተ ፡ (ደጋግሞ ፡ ባሳሰበ) ጊዜ ፡ ፍቺ ፡ በመፍቀዱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ልማድን ፡ የተከተለ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ማስጋቤ ፡ የነበረው ፡ መጠበብ ፡ በነኝህ ፡ የፍቺ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ያለ ፡ ይመስላል ። ሕጉ ፡ መፋታትን ፡ በሚያስከትሉ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ባሉባቸውና ፡ መፋታትን ፡ በማያስከትሉ ፡ የፍቺ ፡ ጉዳዮች ፡ መካከል ፡ ልዩነትን ፡ ያበጃል ። ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ካለ ፡ ፍቺ ፡ በፍጥነት ፡ መሰጠት ፡ አለበት ። ጥፋተኛ ፡ የሆነው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ደግሞ ፡ ቅጣት ፡ ሊጣልበት ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ ፍቺ ፡ እንዲህ ፡ በፍጥነት ፡ ሳይሰጥ ፡ ይችላል ፤ በተጨማሪም ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ ፍቺ ፡ የጠየቀ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ሊቀጣ ፡ ይችላል ።

ስለ ፡ ንብረት ፡ ሕግስ ፡ ምን ፡ አለ ? በልማድ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በተሸጠ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ የተሸጠውን ፡ ንብረት ፡ መልሰው ፡ እንዲያገኙ ፡ የነበራቸውን ፡ መብት ፡ ሕጉ ፡ ይጠብቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ መብት ፡ ሊጠይቁ ፡ የሚችሉትን ፡ ሰዎች ፡ በመግለጽና ፡ በመብቱ ፡ ለመጠቀም ፡ የሚቻልበትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመደርደር ፡ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ ሊያመጣቸው ፡ የሚችለውን ፡ ችግሮች ፡ እንዲቃለሉ ፡ ተደርገዋል ።

ስለ ፡ ሰዎች ፡ ስለቤተዘመድና ፡ ስለ ፡ ንብረት ፡ እንዲሁም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የፈጸመው ፡ ዋና ፡ ሥራ ፤ ጐልቶ ፡ እንደሚታየው ፡ ሁሉ ፡ የልማድ ፡ ደንቦችን ፡ መለወጥ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ማብራራት ፤ ዋናውን ፡ ሁኖቴያቸውን ፡ ማጣራት ፡ እንዲሁም ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በጣም ፡ ትክክለኛ ፡ መስለው ፡ የሚታዩትን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ማዋሃድ ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ በማድረግ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የኤኮኖሚና ፡ የሌላም ፡ ጥቅሞች ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ከፍትሕ ፡ ስሜት ፡ ጋር ፡ የሚስማማውን ፡ ደንብ ፡ በመምረጥ ፡ ሊቀጥል ፡ የማይችለውን ፡ የደንቦች ፡ መደነጋገርና ፡ አለመረጋገጥ ፡ ለማስወገድ ፡ ነበር ።

ከባህል ፡ በተወሰዱት ፡ ደንቦች ፡ ረገድ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የምዕራባውያን ፡ ሕጐች ፡ የሰጡት ፡ አገልግሎት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በይበልጥ ፡ ተስማሚ ፡ መስለው ፡ የሚታዩትን ፡ መፍትሔዎች ፡ አመዛዝኖ ፡ በመምረጥ ፡ ሥራና ፡ በደንቦች ፡ አረቃቀቅ ፡ ዘዴ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሕጉ ፡ ደንጋጌዎች ፡ በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚሰጡትን ፡ መፍትሔዎች ፡ ማለት ፡ የሚወሰዱትን ፡ ቀዳሚ ፡ እርምጃዎች ፡ በማመልከት ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ። በዚህ ፡ አይነት ፡ የተመለከቱት ፡ መፍትሔዎች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከምዕራባውያን ፡ አገሮች ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ያልተመሳሰሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕብረ ፡ ሰብ ፡ ማለፊያ ፡ መስለው ፡ የተገኙ ፡ ናቸው ።

የምዕራባውያን ፡ ሕጐች ፡ አገልግሎት ፡ በይበልጥ ፡ ጠቃሚ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ብቻቸውን ፡ ጠቃሚ ፡ ሆነው ፡ የሚገኙት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ልማድ ፡ ው

ስጥ ፡ ድጋፍ ፡ ባልተገኘላቸው ፡ ባንዳንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች ፡ ነው ። የዚህ ፡ እውነተኛነት ፡ በተለይ ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ በአብዛኛዎቹ ፡ የ፬ኛውና ፡ የ፭ኛው ፡ መጽሐፎች ፡ (ስለግዴታዎች ፡ በጠቅላላና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ውሎች) እንዲሁም ፡ በ፫ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ (ስለ ፡ ንብረት ፡ ) ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብና ፡ ስለድርሰትና ፡ ስለ ፡ ኪን ፡ ጥበብ ፡ ባለሃብትነት ፡ በሚናገ ረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ። በነዚህም ፡ ሕጐች ፡ ረገድ ፡ ከምዕራባውያን ፡ አገሮች ፡ የተወሰደው ፡ በሕግ ፡ አረቃቀቅ ፡ ቴክኒክ ፡ በመልክ ፡ በመልክ ፡ በማደራጀት ፡ ዘዴና ፡ በመምሪያዎች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ። የምዕራባውያን ፡ ሕጐች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ፡እንዳሉ፡ገብተዋል።

እነዚህ ፡ ሕጐች ፡ እንዳሉ ፡ ቢወሰዱም ፡ ቅሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ዎች ፡ ሳይታሰብባቸው ፡ አይደለም ። ይህንንም ፡ በቀላሉ ፡ ለማየት ፡ የሥራዎች፡ አገልግሎት ፡ መስጠትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ የሚለውን ፡ አንቀጽ ፡ በተለ ይም ፡ ስለእርሻ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ የሚናገረውን ፡ የዚህን ፡ አንቀጽ ፡ ምዕራፍ ፡ ማን በብ ፡ ነው ። በኤኮኖሚ ፡ አቋም ፡ በጣም ፡ ለበለፀጉት ፡ የምዕራባውያን ፡ አገሮች ዜጐች ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ለዜጐቿ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ የሕብረ ፡ ሰብ ፡ ደህንነት ፡ ጥበቃ ፡ (ሶሻል ፡ ሲኪውሪቲ ፡ በኔፊት) ፡ እንድታደ ርግ ፡ ያለችበት ፡ ደረጃ ፡ አይፈቅድላትም ። ሕብረ ፡ ሰብንና ፡ ፍትሕን ፡ ለመጠ በቅ ፡ እርምጃዎች ፡ ቢወሰዱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮ ጵያ ፡ ንግድን ፡ እንዳያቋቁሙ ፡ ሊያደርጉ ፡ ይችላሉ ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከሕብረ ፡ ሰብና ፡ ከፍትሕ ፡ ጥበቃ ፡ ይልቅ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ (ካፒታል) ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲገባ ፡ ቅድሚያ ፡ ተሰጥቶታል ። "ሞኖፖሎ ችን ፡ የሚቃወሙ ፡ ሕጐችን ፡ ከማውጣት ፡ በፊት ፡ ሞኖፖሎች ፡ እንዲኖሩ ፡ ያስፈልጋል" እንደሚለው ፡ ትክክለኛ ፡ አነጋገር ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ካሠሪያቸው ፡ ጋር ፡ ባላቸው ፡ የሥራ ፡ ግንኙነት ፡ እንጠብቅ ፡ ብሎ ፡ ከማሰብ፡ በፊት ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ የሥራ ፡ ቦታ ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልጋል ። የማይንቀሳ ቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ ደግሞ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮ ጵያን ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚያስተጋቡ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይገኛሉ ።

በነዚህ ፡ ረገድ ፡ በተለይ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ይስማማሉ ፡ ከተባሉት ፡ ድንጋግ ዎች ፡ በቀር ፡ ኢትዮጵያ ፡ የወሰደችው ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ዘመናዊውን ፡ የምዕ ራባውያንን የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ "መቀበል" የሚለውን ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ማስገባት ፡ ተገቢ ፡ አይሆንም ። ምክንያቱም ፡ ሕጉ ፡ የተ ወሰደው ፡ ከአንድ ፡ የሕግ ፡ መሰናዶ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ የምዕራባዊ ፡ ሕግ ፡ አይ ደለም ። የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ሕግ ፡ ላይ፡ የተመሠረተ ፡ አዲስ ፡ (እንዳለ ፡ ከሌላ ፡ ያልተቀዳ) ሥራ ፡ ነው ። የሕጉ ፡ ዝግጅት በከፊል ፡ አዲስ ፡ ሲሆን ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ደንቦችም ፡ ከልዩ ፡ ልዩ፡ የምዕራባውያን ፡ አገሮች ፡ ሕጐች ፡ በመምረጥና ፡ በጐደለ ፡ በማሟላት ፡ የተወ ሰዱ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ ሕጉ ፡ የተሟላ ፡ እንዲሆን ፡ ስለታሰበ ፡ የብዙ ፡ አገ ሮች ፡ ሕጐች ፡ የተዋሃዱበት ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከአንድ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ የተወሰደ ፡ አይደለም ። እዚህ ፡ ላይም ፡ ቢሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ይዞ ፡ እንዲገኝ ፡ የተፈለገው ፡ የአንድ ፡ አገርን ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ ለአው ሮፓ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ አንድየሆነ ፡ (ዩኒፎርም) ሕግን ፡ ነው ።

በዚህ ፡ የማዋሃድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለአውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ የሆነ ሕግን ፡ ለማውጣት ፡ በየጊዜው ፡ የተደረገቱን ፡ ጥረቶች ፡ ሁሉ ፡ በጥቅም ፡ ላይ

ማዋል ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፤ የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፤ ስለ ፡ ቼክና ፡ ስለ ፡ ሐዋላ ፡ ባለው ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፴ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፴፩ ጄኔቭ ፡ ላይ ፡ ተደርገው ፡ የነበሩት ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ስምምነቶች ፡ ድንጋጌዎችን ፡ እንደወሰደ ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግም ፡ ሮም ፡ ላይ ፡ ስለንብረት ፡ ሽያጭ ፤ ስለ ፡ ስምምነት ፡ ውል ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ሆቴል ፡ ባለቤቶች ፡ ኃላፊነት ፡ ተረቅቀው ፡ የነበሩትን ፡ ተመሳሳይ ፡ ሕጎች ፡ ወስዷል ። በሮም ፡ ላይ ፡ ከተረቀቁት ፡ ሕጎች ፡ የተወሰዱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ትንሽ ፡ የተለወጡት ፡ ባቀራረባቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ ለውጥ ፡ የተደረገው ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ከ፫ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥሮች ፡ በላይ ፡ ስለማይዝና ፡ አንዱ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ደግሞ ፡ በአንድ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ስለ ሆን ፡ እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከአንቀጾቹ ፡ የአጻጻፍ ፡ ፎርም ፡ ጋር ፡ እንዲስማሙ ፡ በማለት ፡ ነው ። በፍሬ ፡ ነገራቸው ፡ በኩል ፡ ለውጥ ፡ የደረሰባቸው ፡ ደንቦች ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ናቸው ።

ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሆነ ፡ ድርጅት ፡ ያዘጋጀው ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ የደንብ ፡ ረቂቅ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮችን ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ በማድረግና ፡ ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ በልጦ ፡ የተገኘውን ፡ በመምረጥ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ ማዘጋጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝ ።

በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ዝግጅት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ምንጮች ፡ ያገለገሉ ፤ የግብጽ ፡ የፈረንሣይ ፡ የግሪክ ፡ የኢጣልያና ፡ የስዊዘርላንድ ፡ አገሮች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ ናቸው ። ስለግዴታዎች ፡ ባለው ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ አንዱን ፡ ሕግ ፡ በሌላው ፡ ለማሟላት ፡ ሲሉ ፡ የመጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ጸሐፊ ፡ የነዚህን ፡ አምስት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሰበሰቡ ። እስከተቻላቸው ፡ ድረስ ፡ ሕጉ ፡ የተሟላ ፡ እንዲሆን ፡ ደከሙ ። ይህንንም ፡ ዓላማ ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ ከነዚህ ፡ የሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ በተጨማሪ ፡ አንዳንድ ፡ ያልተሰናዱ ፡ ደንቦችንና ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉ ፡ ማብራሪያዎችን ፡ ተመልክተዋል ። በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ጐድሎው ፡ የሚገኙትን ፡ ነገሮች ፡ ለማስተካከል ፡ ብሔራዊ ፡ የሆኑ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፡ ወይም ፡ የሊቃውንት ፡ ጽሑፎች ፡ ስለሌሉ ፡ እነዚህን ፡ ደንቦችና ፡ የሕግ ፡ ማብራሪያዎች ፡ መመልከት ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውሉ ፡ የማይችሉ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ የያዙ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆኑ ፡ ጥቃቅን ፡ ልዩነቶችን ፡ የሚፈጥሩ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ የዚያውን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሁኔታ ፡ የማይመለከቱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ከሕጉ ፡ ለማስወገድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕጉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አላመነቱም ።

እላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ ሁሉ ፡ የተመለከትናቸው ፡ ሕጉ ፡ ምን ፡ ነገሮችን ፡ መያዝ ፡ እንዳለበት ፡ ለማየት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሊሰጣቸው ፡ ስለማይገባቸው ፡ መፍትሔም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሙሉ ፡ እንዲተያዩ ፡ ልዩነታቸውም ፡ እንዲታወቅ ፡ ተደረገ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ እንዲሁም ፡ ዘመናዊ ፡ ዝንባሌዎች ፡ በመመልከት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ የሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ ውስጥ ፡ ከየትኛውም ፡ ቢወሰድም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊመረጥ ፡ የሚገባው ፡ ፎርሙላ ፡ ተፈለገ ። በእውነትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ው

ስጥ ፡ አንድ ፡ አንቀጽ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ ካንዳችም ፡ አንቀጽ ፡ ጋር ፡ ጭራሽ ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ የአንቀጾችን ፡ የጽሑፍ ፡ አቀራረብና ፡ የቃላትን ፡ ምርጫ ፡ እንዲመሩ ፡ የተደረጉት ፡ ደንቦች ፡ በሙሉም ፡ ባይሆን ፡ በብዛት ፡ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ጸሐፊዎችን ፡ በሌላ ፡ አገሮች ፡ የሚጠቀሙባቸውን ፡ ፎርሙላዎች ፡ እንዲያስወግዱ ፡ አድርገዋቸዋል ።

ከሁሉም ፡ የሚበልጡትን ፡ የሕግ ፡ ደንቦች ፡ ለማግኘት ፡ የተደረገው ፡ ፍለጋ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሕጎች ፡ በመመርመርና ፡ በማወዳደር ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ አልነበረም ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ሕጎች ፡ የተደረገው ፡ ምርምር ፡ ቀጠለ ፤ በተለይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ አንቀጾች ፡ በእንግሎ ፡ አሜሪካን ፡ ሕግ ፡ የተነሳሱ ፡ ናቸው ። ለዚህም ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑት ፡ ውልን ፡ ባለመፈጸም ፡ ምክንያት ፡ የሚከፈለውን ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ አወሳሰን ፡ "በአዕምሮ ፡ ግምት ፡ ትክክለኛ ፡ ጊዜ" የሚለውን ፡ አሳብ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መጠቀሱ ፡ እንዲሁም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርሱ ፡ ኃላፊነቶች ፡ የሚናገሩት ፡ ደንቦች ፡ ናቸው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በጠቅላላ ፡ እነጋገር ፡ በግዴታዎች ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ዋናው ፡ ምንጭ ፡ የስዊስ ፡ ፌዴራል ፡ የግዴታዎች ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ከሌሎች ፡ አገሮች ፡ ሕጎች ፡ ጋር ፡ ሲወዳደር ፡ በዕድሜ ፡ ገፋ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ በእኛ ፡ አስተያየት ፡ አስደናቂ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ያገኘነው ፡ እንዲሁም ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ ምንጭ ፡ ያገለገለ ፡ የፈረንሣይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ መደንገግ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በታየን ፡ ቦታ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አስፈላጊው ፡ ድንጋጌ ፡ ባልወጣበት ፡ ረገድ ፡ ጠቃሚ ፡ ሆን ፡ ያገኘነው ፡ የፈረንሣይ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ። ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኃላፊነት ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ የተዘጋጀው ፡ መስዬ ፡ ሮዴር ፡ በደረሱት ፡ "ላ ፡ ሬስፖንሲቢሊቴ ፡ ሲቪል" በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ በመጠቀም ፡ ነው ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቀሙትን ፡ ሀብቶች ፡ በማስለቀቅ ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ ሲጻፍ ፡ ደግሞ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ የመስዬ ፡ ዋሊን ፡ መጽሐፍ ፡ 'ድሯ ፡ አድሚኒስትራቲፍ' ነው ። እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ስለሚያደርጓቸው፡ ውሎች ፡ ሕግ ፡ ለማዘጋጀት ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ የመስዬ ፡ ደ ፡ ሉባዴር ፡ መጽሐፍ ፡ "ትሬቴ ፡ ቲዎሪክ ፡ ኢ. ፕራቲክ ፡ ዴ ፡ ኮንትራ ፡ አድሚኒስትራቲፍ" ነው ። ሌሎች ፡ ሕጎች ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡ አላበረከቱም ። የኢጣሊያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ አሳብ ፡ ይዞታ ፡ በጣም ፡ የከረረና ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሮችን ፡ የሚመለከት ፡ መስሎ ፡ ታዬን ። የግሪክ ፡ አገር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚደነግገው ፡ በሕሊና ፡ አስተሳሰብ ፡ መሠረት ፡ መስሎ ፡ ታዬን ። የግብጽ ፡ አገር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ መሰለን ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የዘረዘርናቸው ፡ ትችቶች ፡ የእነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ነቀፌታ ፡ አይደሉም።ምክንያቱም ፡ በሚያገለግሉበት ፡ አገር፡ እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የምናትተው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ የገጠመንን ፡ ችግር ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የጀርመን ፡ አገር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (ቢ-ጂ-ቢ-) በዝግጅቱ ፡ በኩል ፡ ታላቅ ፡ አድናቆትን ፡ ያተረፈ ፡ ቢሆንም ፡ ተመሳሳይ ፡ ምክንያቶች ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ እንዳንጠቀምበት ፡ አደረጉን ።

ግዴታዎችን ፡ ከሚደነግገው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ በስተቀር፡ በሌሎች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ምንጮች ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ተደርጓል ። ስለ ፡ ውርስ ፡ ለተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የሆኑት ፡ የፖርቱጋልና ፡ የእስራኤል ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ረቂቆች ፡ ናቸው ። ስለ ፡ ውሃ ፡ ባለሃብትነት ፡ ለተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ደግሞ ፡ ከቀድሞው የቱርክ ፡ አገር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (ማጀል) እና ፡ ከኢራን ፡ አገር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ወስደናል ። ስለ ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ የሚደነግገውን ፡ የሩሲያን ፡ ሕግ ፡ እንኳ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ አውለናል ። እንዲሁም ፡ መሬት ፡ እንዴት ፡ በሕብረት ፡ ሊገለገሉበት ፡ እንደሚቻል ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ ለማቋቋም ፡ ሲባል ፡ የሩሲያ ፡ የሕብረት ፡ እርሻን ፡ (ኮልኮሆዝን) የሚገልጽ ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ውሏል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ክፍል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ እንዲተው ፡ ተደረገ ። ዶማሬሬግሊርና ፡ የተባለውን ፡ የስዊድን ፡ አገር ፡ ልማድ ፡ በመከተል ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ "ለዳኞች ፡ የሚሆኑ ፡ ደንቦች" በሚል ፡ አርእስት ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረታዊ ፡ ሃሳቦችን ፡ በመቅድም ፡ መልክ ፡ ለማቅረብ ፡ የነበረው ፡ ሐሳብ ፡ እንዲቀር ፡ ሆነ ። ይህ ፡ ሐሳብ ፡ በስዊድንም ፡ ሕግ ፡ ከተተወ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ አልፈዋል ።

በመጨረሻም ፤ ጥቂቶች ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባሕሎች ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ እንዳለመመርኰዛቸው ፡ (እንዳለመመሥረታቸው) አዲስ ፡ ያፈለቅናቸው ፡ እንጂ ፡ ከሌላ ፡ ያልታቀዱ ፡ መሆናቸውን ፡ በጭማሪ ፡ ለመግለጽ ፡ እንወዳለን ። በተለይም፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ ስለ ፡ ውሃ ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገቦች ፤ ከዚህም ፡ ባነሰ ፡ ሁኔታ ፡ ስለማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ አሳዳሪነትና ፡ ስለ ፡ ኑዛዜዎች ፡ ያለውን ፡ የድንጋጌዎች ፡ አቀነባበር ፡ ሳንጠቅስ ፡ አናልፍም ። በነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ረገድ ፡ ደንቦችን ፡ ማውጣት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባሕሎች ፡ ጽኑ ፡ መሠረት ፡ አላበረከቱም ። የምዕራባውያን ፡ አገሮች ፡ ደንቦችም ፡ ተስማሚ ፡ ሆነው ፡ አልተገኙም ። አዲስ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ አስፈለገ ። ለሕጉ ፡ ፀሐፊዎችም ፡ ይህ ፡ ሥራ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተዋህዶ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችል ፡ መስሎ ፡ ታያቸው ።

የሕጉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አንቀጾች ፡ እንደተረቀቁ ፡ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ጸሐፊ ፡ አንቀጾችን ፡ የሚያብራራ ፡ አንድ ፡ ሐተታ ፡ አዘጋጀ ። ይህም ፡ ሐተታ ፡ የመጀመሪያውን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ መሠረት ፡ ከመግለጹም ፡ በላይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አንቀጾች ፡ ለማርቀቅ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉትን ፡ ምንጮች ፡ አመለከተ ። በዚህም ፡ መንገድ ፡ እነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ ከየት ፡ እንደመነጩና ፡ ምን ፡ ለውጥ ፡ እንደደረሰባቸው ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ ለማሳየት፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ይሆናል ። የሚያሳዝነው ፡ እነዚህ ፡ ሐተታዎች ፡ ሳይታተሙ ፡ መቅረታቸው ፡ ነው ። በመጀመሪያ ፡ ስለተረቀቁት ፡ አንቀጾች ፡ የቀረቡት ፡ ሐተታዎች ፡ በመጠኑ ፡ የተሟሉ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፤ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለ ፡ ትርጉሙ ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ ሊፈጽም ፡ የማይችል ፡ መስሎ ፡ ስለታየና ፡ እንዲሁም ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ በይበልጥ ፡ ያሰበበት ፡ በቀረበው ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ ሕጉ ፡ ከየት ፡ እንደመነጨና ፡ በምንስ ፡ መንገድ ፡ እንደተዘጋጀ ፡ ሆኖ ፡ ስላልተገኘ ፤ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ሐተታዎቹ ፡ አጠር ፡ እያሉ ፡ እንዲጻፉ ፡ ሆነ ። በኢትዮጵያ

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጾችና ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጎች፡ አንቀጾች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ተመሳሳይነት ፡ የሚያሳይ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ለማውጣት ፡ ታስቦ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሰንጠረዥም ፡ ሕጉ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ሲታተም ፡ አብሮ ፡ ይታተማል ፡ የሚለው ፡ አሳብ ፡ ተቀባይነት ፡ ሳይኖረው ፡ ቀረ ። ይህም ፡ ትክክለኛ ፡ አስተያየት ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ሰንጠረዥ ፡ ስለ ፡ ሕጉ ፡ በተጻፈ ፡ ሐተታ ፡ ውስጥ ፡ ቢገባ ፡ ቦታ ፡ ይኖረው ፡ ይሆናል ፤ በአፊሴል ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ቦታ ፡ የለውም ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ጽሑፍ ፡ በአማርኛ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ታስቧል ። እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጽሑፍ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ አስፈላጊ ፡ መሙያ ፡ ነው ። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎችን ፡ ሕጉን ፡ በሚተረጉሙበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲረዱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ስላገለገሉት ፡ ነገሮች ፡ በይበልጥ ፡ የተሟሉና ፡ ትክክለኛ ፡ የሆኑ ፡ መምሪያዎችን ፡ ይይዛል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ። እነርሱም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የተነጻጸሩ ፡ ሕጎች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ መሆኑን ፡ ለማየት ፡ ያስችላሉ ።